# የኤም ኤል ኤን በሽታን በአርሶ አደሩ ማሳ ላይ ለመቆጣጠር እንዲቻል የሚወሰዱ አስራ ሁለቱ እርምጃዎች

## ኤም ኤል ኤን በሽታ ምንድን ነዉ?

- ኤም ኤል ኤን በሽታ በቆሎን የሚያጠቃ የቫይረስ በሽታ ነዉ፡፡
- የኤም ኤል ኤን በሽታ መንስኤ የሜሽ ክሎሪቲክ ሞታል ቫይረስ ከሌላ ቫይረስ ለምሳሌ ሹገርኬን ሞዛይክ ቫይረስ ፣ሚዝ ዱዋርፍ ሞዛይክ ቫይረስ ፣ወይንም ከዊት ስትሪክ ሞዛይክ ቫይረስ በጋራ የሚከሰት በሽታ ነዉ፡፡
- በአፍሪካ በሽታዉ ለመጀመሪያ ጊዜ ሪፖርት የተደረገዉ በመስከረም 2011 በኬኒያ ሲሆን ከዚያም በታንዛኒያ፣ኡጋንዳ፣ሩዋንዳ፣ኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ፣በደቡብ ሱዳን እና በኢትዮጵያ በ2014 ተከስቷል፡፡
- የኤም ኤል ኤን በሽታ ለበቆሎ አመራረት ከፍተኛ ተግዳሮት ያለዉና መቶ ፐርሰንት የምርት ብክነትን ስለሚያሰከተል ለምስራቅ አፍሪካ የምግብ ዋስትና ስጋት ነዉ፡፡

## የኤም ኤል ኤን በሽታ ምልክቶች እና የመተላለፊያ መንገዶቹ

### የኤም ኤል ኤን በሽታ ምልክቶች፡



ቅጠሎቹ በከፍተኛ ሁኔታ መጎዳት በበሽታዉ የተጠቁ የበቆሎ ቅጠሎች የክሎሮስስ ወይንም ኒክሮሲስ ሊኖራቸዉ ይችላል

መካንነት ወይንም የአበባ ዱቄት አለማምረት





በጣም አናሳ ወይንም ምንም የበቆሎ ፍሬ አለመያዝ

የበቆሎዉ ልባስ ያለጊዜዉ መድረቅ





ግንዱ(ቅጠል የሚወጣበት የተክሉ ክፍል) ማጠር ፤ ድንክ መሆን

የበቆሎ ፍሬ የመሞት ምልክት (የኒክሮሲስ ቅጠሎች ፤ ማዕከላዊ ክፍል መመንመንና መድረቅ)



### የኤም ኤን አል በሽታ እንዴት ይዛመታ ?

ነፍሳቶች(ተሸካሚ ነፍሳት) የኤም ኤን አል ቫይለስን ሊያስተላልፉ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል (ትሪፕስ፣ አፊድስ፣ጢንዚዛዎን እና የስራስር ትሎች) ይገኙበታል፡፡



ትሪፕስ

አፊድስ

የኤም ኤን አል በሽታ ዘር ወለድም ሊሆን ይችላል(ማለትም ከተበከለ ተክል የተገኘ ዘር በዉስጡ ቫይረሱን ሊይዝ ይችላል፡፡




እንስሳት ፣ሰዎች ፣ የእርሻ መገልገያ ማሽነሪዎችና ቁሳቁሶች ከተበከለ የእርሻ መሬት ወደሌላኛዉ በእንቅስቃሴ ወቅት ለያሰራጩ እና የብክለት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡




AGRA Growing Africa's Agriculture
CIMMYT International Maize and Wheat Improvement Center
AATF PROSPERITY THROUGH TECHNOLOGY

# የኤም ኤል ኤን በሽታ እንዳይሰራጭ አርሶ አደሮች እንዴት መከላከል ይችላሉ?

## አርሶ አደሮች የሚከተሉትን አስራ ሁለት እርምጃዎች በመከተል የበሽታዉን ስርጭት ማስቀረት ይችላሉ

**1.** መሬቱን ከመዝራት በፊት የመሬቱን የአስተራረስ እና የበሽታ ታሪክ ማጥናት፡፡አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ አፈራርቆ መዝራት፡፡




**2.** የእርሻ መሬቱ ላይ ያለዉ አፈር ሁሌም ለም መሆኑን ማረጋገጥ፡፡ ይህም አዝርዕቱ ጤናማ እንዲሆኑና በሽታን እንዲቋቋሙ ይረዳቸዋል፡፡




**3.** ሁሌም ማረጋገጫ የተሰጠዉን ዘር መጠቀም፡፡ ዘርንም በተደጋጋሚ አለመጠቀም፡፡





**4.** እህልን እንደ ዘር አለመጠቀመ፡፡



**5.** ማንኛዉንም የእርሻ መሳሪያ ከተጠቀሙ በኃላ በአግባቡ ማጽዳት የበሽታዉ አምጭ ቫይረስን መዛመት ያስቀራል፡፡



**6.** ዝናብ መዝነብ እነደጀመረ ቀድሞ መዝራት፡፡



**7.** ሳርና አረም ለቫይረሱ እንዲሁም ለበሽታ አስተላላፊ ነፍሳት መደበቂያ ሊሆኑ የሚችሉ ስለሚችሉ በእየጊዜዉ በማስወገድ የማሳዉን ጽዳት መጠበቅ፡፡




**8.** የበሽታ አሳተላላፊ ነፋሳት በማሳዉ መከሳታቸዉን ለማወቅ በእየሳምንቱ መከታተል፡፡ የነፍሳቶች በብዛት መገኘት በበሽተታ የመጠቃት እድልን በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል፡፡



**9.** የሚመከሩ የተባይ ማጥፊያዎችን በመጠቀም የበሽታ አምጭ ነፍሳትን በኬሚካል መቆጣጠር እንደሚቻል ያስታዉሱ(በሳምንት ወይንም በሁለት ሳምንት አንዴ ይጠቀሙ)



**10.** የኤም ኤል ኤን በሽታ ምልክቶችን መከታትል ቶሎ ሁኔታዉን ተገንዝቦ መፍትሄ ለመፈለግ ይረዳል፡፡




**11.** የኤም ኤል ኤን ምልክት የታየባቸዉን ተክሎች በቶሎ በመንቀልና ከማሳዉ ዉጭ ማቃጠል ወይንም መቅበር የበሽታዉን ስርጭት ለመቀነስ ይረዳል፡፡ በኤም ኤል ኤን የተጠቃ ተክልም ሆነ የግጦች መሬት እንስሳት እንዳይጠቀሙ ማድረግ ፡፡





የጥራ ጥሬ ሰብሎችን (ባቄላ፣አኩሪ አተር ፣ አተር) በማብቀል በማፈራረቅ መዝራት፡፡በተደጋጋሚ በቆሎን ኣለመዝራትና ያለበቆሎ ቢያንስ ሁለት ወራት የሚቆይበትን የአሰራር ሁኔታ ማመቻቸት፡፡



Alliance for a Green Revolution in Africa (AGRA)
P.O. Box 66773 Westlands 00800, Nairobi, Kenya
Phone : +254 (20) 3675 000 | +254 703 033 000
www.agra.org

International Maize and Wheat Improvement Center (CIMMYT)
Dr. Suresh, L.M. | Maize Pathology Lead – sub-Saharan Africa
Email : l.m.suresh@cgiar.org
Phone : +254 702 392 664
www.cimmyt.org

African Agricultural Technology Foundation (AATF)
P O Box 30709 - 00100, Nairobi, Kenya
Phone: +254 (0) 20-4223700
Email: aatf@aatf-africa.org
www.aatf-africa.org